# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 33 ታሕሣሥ 23 2001 ዓ.ም


**አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!**




## ፋሽስታዊ አገዛዝ በንጹህን የዲሞክራሲ ታጋዮች ላይ!

በአንጋፋው ምሁር እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ፕሮፌሰር መስፍን ላይ የደረሰው ድብደባ እና ከፍተኛ ዘለፋ የገዢው ቡድን ምንም ኢትዮድያዊ ባህሪ እንደሌለው እና ፋሺስታዊ ባህሪዉን አጎልቶ ያሳየ ክሰተት እንደነበር ተጠቆመ። በጅማ ዩኒቨርሲት የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪ የሆኑት ስማቸው እንዳይገልጽ የጠየቁት ምሁር ኢትዮያዊያውን በአለም የምንታወቅበት ልዮ የሆነ ማንም የሚያከብረው የስነምግባር መመሪያ አለን። ከነዚህ የስነምግባር መመሪያዎች አንዱ ታላላቆችን እና ሽማግሌዎችን ማክበር የሚለው ዋናው ነው። ለአረጋዊ ያን ከፍተኛ ክብር በሚሰጥ ህዝብ ውስጥ ወያኔ በአደባባያ አዛውንቱን ፕሮፌሰር በአጸያፊ ቃላት መዝለፉ እና መደብደቡ ፋሺታዊ ባህሪውን ከማጉላቱ እና የኢትዮድያን ባህልና እሴት ጥላቻና ንቀት እንዳለው ከማሳየቱም ባሻገር ከፍተኛ የፓለቲካ ሽብር ለማንገስ ቆርጦ መነሳቱን እንደሚያመለክት አስረድተዋል። እንደ ምሁሩ ገለጻ ለማስተላለፍ የተፈለገው መልእክት “እንኳን ላንተ ወይም ላንቺ ቀርቶ አለም የሚያውቀውን ሰው መደብደብ፤ ሽማግሌም ቢሆን ማዋረድና መዝለፍ ስለምንችል በጭራሽ ሌላ ነገር እንዳታስቡ እርቃችሁ ተቀመጡ” የሚል እንደሆነ ተገልጿል።

በከተማ አውቶቢሶች አውዛውንቶች ሲያይ ወጣቱ ሳያንገራግር መቀመጫውን ለቆ አዛውንቱን በሚያስቀምጥበት ሀገር፡ ለእድሜ ባለጸጋዎች በሄዱበት የአገልግሎት መስጫ እና ሌሎች ቦታዎች ሁሉ ቅድሚያ በሚሰጥበት ሀገር ፕሮፌሰር መስፍንን በመሰለ የተከበሩ አዛውንቶች ላይ የሚወሰደው እንግልትና የማዋረድ ተግባር የወያኔ ባለሥልጣናት አረመኔያዊ ድርጊት ገደብ እንደሌለው አመላካች ብቻ ሳይሆን ቁጭ ብሎ ለተመለከተ በእንዲህ ዓይነት ግብዑዝ ፍጥረታት ለ18 ዓመታት ከመገዛት የባሰ አዋራጅና ሂሊናን ሊሰቀጥጥ የሚገባ ነገር መኖር አልነበረበትም ተብሎአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

በቁጥራቸው በጣም ጥቂት የሆኑ ጸረ - ኢትዮጵያ ዘረኞች፣ በሚሊዮኖች የምንቆጠረውን አዋርደው ለመግዛት የበቁት፣ ዛሬም የስልጣን እድሜያቸውን በማራዘም፣ ጸረ ሃገር አጀንዳቸው ማስፈጸም የሚችሉት የተቀረነው ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነትና ለሃገራችን ደህንነት የምንቆረቆረው ብዙሃኑ የሃገሪቱ ዜጎች አምረን ልንታገላቸው ባለመቁረጣችን ብቻ ነው።

ይህ ትግል ተጀምሯል። ሁሉም የድርሻውን ለማበርከት እየተነሳ ነው። ከመሃላችን ውድ ህይወታቸውን ለመሰዋት ቆርጠው የተነሱ አሉ።

በውጭ ሃገር ከምንገኘው የሚጠበቀው በሕይወታቸው ለቆረጡት የአቅማችንን መደገፍ ነው።

ከእርስዎ የሚጠበቀው የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነው። ሌሎች፣ ኢትዮጵያችንን በህይወታቸው ሊታደጓት ሲነሱ የእርስዎ የገንዘብ እርዳታ ለኢትዮጵያ ሲያንሳት ነው። እኛ ፈዘን ስናቀላፋ የኢትዮጵያ ጠላቶች ያካበቱት ሃብት ብዙ ነው። እነዚህን ዘረኞች ለመታገል፣ ሳንቲም ተለቅሞ አይሆንም። ሁሉም ቀበቶውንና መቀነቱን ጠበቅ አድርጎ ወንዝ የሚያሻግር መዋጮ ማዋጣት ይኖርበታል።

ግንቦት 7 ንቅናቄ በአለም ላይ ከተበተነውና ኢትዮጵያን ከሚወደው እያንዳንዱ ዜጋ 500 የአሜሪካ ዶላር ለማሰባሰብ እቅድ አውጥቷል።

ይህ መዋጮ የወያኔ/ኢህዴግን መጨረሻ ማስጀመሪያ ይሆናል ብለን እናምናለን። ማስጨረሻው ግን ከእዚህም በላይ እንደሚሆን አውቀን ልንዘጋጅ ይገባናል። ምርጫችን ከእነዚህ ዘረኛ አምባገነን ሃይሎች ለመገላገል መክፈል የሚገባንን መስዋእትነት መክፈል ወይም በገዛ ሃገራችን ተዋርደን መኖርና የሃገራችንን ውድምት በጸጋ መቀበል ነው። ይምረጡ! ምርጫዎት ኢትዮጵያና ነጻነት ይሁን። የግንቦት 7 ንቅናቄን የገንዘብ አቅም ለማጎልበት ወገኖችዎትን አስተባብረው ይነሱ። በአስተዋጽዎ ግንቦት 7 ያዘጋጀውን የአርበኝነት የእውቅና ሰነድ የርስዎ ያድርጉ፡፡ ይህ የውርደት ቀን ሲያበቃ፣ ማብቃቱ ደግሞ አይቀርም፣ እኔም ታሪክ ሰርቻለሁ ለማለት ከሚታደሉቱ አንዱ ይሁኑ።




## ማስታወቂያ

**በውጭ ሃገር የሚኖሩ ልጆች፣ ቤተሰብ ዘመድ ጓደኛ አለዎት?**

ዛሬ በሃገራችን ላይ በተንሰራፋው ዘረኛ ዘራፊና አምባገነን አገዛዝ ተንገሸግሸዋል? ይህ አገዛዝ ለኢትዮጵያችን አይመጥናትም፣ ከነግስንገሱ መጠረግ አለበት ብለው ያስባሉ?

ይህን የሚያስቡ ከሆነ፤ እኛም በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ ጥላ ስር የተሰባሰብን ወገኖችዎ የምንለው ይህንኑ ነው። እዛው አጠገብዎ የሚኖረው ሌላው የግንቦት 7 አባልና ደጋፊ የሚለው ይህንኑ ነው። እንግዲህ ሁላችንም ይብቃን ብለናል።

የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አገዛዝ እድሜ በማሳጠርና መራዘም መሃከል ያለው ልዩነት ወያኔን ለማስወገድ ሕይወቱን ለመስጠት የቆረጠ ጀግና ማጣት የህዝብ ምሬት ማነስ አይደለም። መለስ ዜናዊ እንዳሻው ከሚያዛቸው ደናቁርቶች በላቀ እውቀትና ጥበብ የሚመራና የሚያደራጅ ሃይል የመፍጠር ችግር አይደለም። ይህንን ግንቦት 7 በሚገባ አሟልቶታል የበለጠ የሚያሟላው ነው። የሚጎድለው የነጻነቱን ንቅናቄ በሁሉም ቦታ ለማቀጣጠል የሚያስችሉንን ግብአቶች የሚሟላት ችግር ብቻ ነው። ግንቦት 7 ለወጠነው ሁለገብ ትግል ማካሄጃ የሚሆን ታለቅ የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ በቅርቡ ጀምሯል። ይህንን የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ እንዴት በሃገር ቤት እንደምናከናውን በያላችሁበት የሚገልጹላችሁ ሰዎች መድበናል።

በውጭ ሃገራት ለምናደርገው የገንዘብ ማሰብሰብ ስራ እርስዎ በቀላሉ ብዙ ማበርከት የሚችሉበት መንገድ አዘጋጅተናል። ልጆችዎ፣ ቤተሰብዎ፣ ዘመድና ጓደኛዎ ስልክ ሲደውሉ ወይም ደብዳቤ ወይም ኢሜል ሲጽፉ ይንገሯቸው። ወያኔ፤ ኢህአዴግን ምን እንደሚገባው ያስረዷቸው። ለኔ ስልክ በመደወል ሰቆቃየን በማዳመጥ የምታጠፉትን ገንዘብ፣ እዚህ እየተመላለሳችሁ በአሳር ያገኛችሁትን ዶላር፣ ዩሮና ፓውንድ ደማችን ለሚመጡ ዘረኛ ዘራፊዎች አስረክባችሁ ከምትሄዱ እዛው ለግንቦት 7 አዋጡት ተደጋግፋችሁ ለሁላችንም ነጻነት ተግተው ይስሩ ይበሏቸው። ዛሬ ስልጣን ላይ ያሉት ዘረኞች ለእኩይ አላማቸው ካሰባሰቡት ሃብት፣ እውቀትና ጉልበት በላይ ለነጻነትና ለሃገር ህልውና ማሰባሰብ እንደምትችሉ እናንተ የኢትዮጵያ ልጆች ተባብራችሁ አሳዩዋቸው ይበሏቸው። አይርሱ። የእርስዎ አንድ መልእክት የሁላችንንም የነጻነት ቀን የሚያቀርብ አንድ እርምጃ መሆኑን ያስታውሱ!

**ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ**

# የጀግናይቱ የመጨረሻ ቃል!



"በእኔ እምነት ይሄ ሁሉ ከሕግ የወጣ ዛቻና ማስፈራሪያ እየደረሰብን ያለው ስለ ቃላት ጨዋታ ወይም ስለ ተዛባ እውነት ወይም ስለተጣሰ ሕግ አይመስለኝም። መልዕክቱ ግልጽ ነው። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሠላማዊ ታጋዮች። "በሠላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ማድረግ የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ በተሰመረው መስመር ሳይሆን፤ ገዢው አካል ወይም ግለሰቦች በፈቀዱት ብቻ ነው" የሚል ነው። ለዚህም ደግሞ "እሺ" ወይንም "አዎ" ማለት ለእኔ እጅግ ከባድ ነው።"

ብርቱካን ሚደቅሣ፣ ታህሳስ 18 ቀን 2001 ዓ.ም

ወርቅን በእሳት እንዲሉ፣ የኢትዮጵያ ታጋዮች ደግሞ የሚፈተኑት በህሊናቸው ሆኗል። ፍቅርን መቻቻልን ሰብከው፣ በጨለማ ግርዶሽ ውስጥ ብርሃንን ፈልገው፣ በእብሪተኞች አምባ ውስጥ ሰላም ሽተው ሲነፈጉ፣ ጀግኖች የመጨረሻው ግብግብ ውስጥ ይገባሉ። ከውስጥ በሚወተውታቸው የፈጣሪያቸው ክፉይ በሆነው የህሊና ሚዛናቸውና፣ ማሰላሰል ማበላለጥ መብከንከን፣ ወደስጋው ማድላት በሚወደው አእምሯቸው መሃል የጦርነት አውድማ ይሆናሉ። ወደ ስጋቸው ሲያደሉ የፍርሃት፣ የአድርባይነት፣ የንቅዘት መደበሪያ ይሆናሉ። ሰውነታቸው እንኳንስ ለራሳቸው ከፋቅ ለሚያያቸው እንኳ ይከረፋል ። በአንፃሩ ህሊናቸው የግብግቡ አሸናፊ ሆኖ ሲወጣ፣ ውሳኔያቸው ጨለማ ውስጥ የሚያስወረውር፣ ወፌ-ኢላላ የሚያስገርፍ እንኳ ቢሆን፣ አበባቸው ከሩቅ የሚያውድ ፅጌረዳ ይሆናሉ። በብርቱካን የመጨረሻ ቃል የሆነውም ይሄው ነው። ከፍሬው በፊት የሚያብበው አበባ፣ ከአዝመራው በፊት የሚያሸተው እሸት ነው ፈክቶ ሃገሪቱን በብርቱካን ሽታ ያወደው። የዘረኝነትን ክርፋት፣ በኢትዮጵያዊት ፅጌረዳ ሽቱ ሃገር ምድሩን ያስጌጠው። የእረኝነትን ተራ ጥጋብ፣ በማይበገር የዕውነት ወላፈን ያቀለጠው። ጀግናይቱ ብርቱካን ለአለሙ ያስረገጠችው ነገር ቢኖር፣ እመ ሃገር ኢትዮጵያ የወላድ መካን አለመሆኗን ብቻ ሳይሆን፣ የቡከን ዘረኞችን የእብሪት እርምጃ እንኳንስ ልንበረከክለት፣ ልንፈራው እንኳ እንዳይቻለን በነፃነት ታሪክ የተገመደ የሃቅ ክታብ በአእምሯችን ያሰርን መሆናችንን ነው። የእናትነት ፍቅር የሚጎድልባትን የሴት ልጇን ተስፋ፣ ጠንካራ አመራርዋን የሚሻውን የሊጋ ፓርቲዋን እድል፣ እንደ ወጣት የህግ ሰው ሊደርሳት የሚችለውን የግል ህይወት ጥቅም ሁሉ እርግፍ አድርጋ አእምሮዋን ለህሊናዋ ስታስገዛና፣ እምቢ ለነፃነት ስትል፣ "ዛሬ ደመቅሽ አበባዬ" ብለን የሙሽራ ዘፈን ብንዘፍንላት፣ ከዛሬው ብካይ አድማስ ባሻገር የምናየው የዘረኝነት ክስመት አይቀሬነት እንደ ንጋት ፀሀይ ከተራሮቹ በስተጀርባ ተጋርዳ ስለምትታየን ነው።

የብርቱካን ፀሀይ "ለሰላማዊ ታጋዮች" ሁሉ ሃቁን ፍንትው አድርጋ እንደምታሳያቸው ተስፋችን ነው። በእርግጥም "ስለተዛባ እውነት ወይም ስለተጣሰ ሕግ" አይደለም ወያኔ የተጨነቀው። መሪዬ ብሎ በጎለተው ተራ ባለጌ እልህና፣ ሊሰበር የማይችለውን የኢትዮጵያ ቅስም ለማነካከት በሚያደርገው ቀቢፀ ተስፋ የሚደርሰውን ጥፋት ፈርቶ አንገትን መድፋት፣ ወይም በህሊና ሃቅ ክፋትን ለመጋፈጥ በቁርጠኝነት በመቆም መሃል ምርጫው የማያደናግር ሆኖ ተገትሯል። "በሰላማዊ ትግል" ስም ትግልን ሳይሆን ዝናን የሚሹ ካሉ ጊዜው አሁን አለመሆኑንና፣ የህዝቡ የትግል መንፈስ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ከሚቸልሱ ወደግል ኑሮአቸው ቢመለሱ የሚሻል መሆኑን አውቀው ቢሰበሰቡ የተሻለ ነው እንላለን። "ለሰላማዊ ታጋዮች" ሁሉ የቀረበላቸውም ምርጫ፣ ወይ ሰላማዊ ትግሉ የሚጠይቀውን ወኔ ይዘው በብርቱካን ብርሃን መጓዝ፣ አለያም ብርቱካንን አውግዘው ለዘረኞች "ሰላም" መንበርከክ ሆኗል። በብርቱካን ብርሃን እንዲመሩ ተስፋችን ነው። ከእስር እንድትፈታ አበክረው እንዲታገሉና፣ ህዝቡንም በሰላማዊ እምቢተኝነት እንዲያታግሉ ምኞታችን ጭምር።

በመጨረሻ ቃሏ ብርቱካን ስለ ሽማግሌዎቹም ሚናና ስለሚያውቋቸውም ሃቆች ተናግራለች። ብርቱካን በሰጠችው ቃል "ሽማግሌዎቹ ሌሎች የመግባቢያ ሃሳቦችን ወደኋላ የተተወ ቢሆንም በሀገራችን ባህል ይቅር በመባባል መንፈስ የተቃኘውን ያንን ሰነድ ብንፈርም ጉዳዩ ባለበት ደረጃ እንደሚቆም ፋይሉም እንደሚዘጋ ገልጠው ሽምግልናውን ገፉበት። ቃል በቃል በመግለጽም ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ይህ ሰነድ ከተፈረመ የሥራ አስፈጻሚ ሥልጣኔን ተጠቅሜ ክሱ እንዲቋረጥ አደርጋለሁ" እንዳሉ አረጋገጡልን" ብላለች። የዚህን ቃል ዕውነትነት የጉዳዩ ባለቤት የነበርነው የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር አባላት መሃልም ያለነው እንመሰክራለን። በመንፈስ አባትነት መታየት የሚፈልጉት ሽማግሌዎችስ ይህን የሃቅ ዕዳ እንዴት ሊሸከሙት ይሆን? በዚህ ጉዳይ ላይ ለሃቅና ለፈጣሪያቸው በህዝብ መድረክ ምስክርነታቸውን ሳይሰጡ፣ በሽምግልና ስም መቀጠል አይቻላቸውም እንላለን። "ታጋይ ነበርን ሁለቱንም ወገን ለማቀራረብ ልንጠቅም እንችላለን" ብለው ሽምግልናውን የተቀላቀሉ፣ በሽምግልና ስም ከአሜሪካ ድረስ ሄደው፣ ሽምግልናን ከገዢው ፓርቲ ባለስልጣናት ጋር መወዳጃና ከራሳቸውም አልፈው ሌሎችን "የከተማ መሬትና የባንክ ብድር እናሰጥሃለን" ማባበያ ለወያኔ የፖለቲካ ድጋፍ ለመሸመት ላይ ታች ማለት የጀመሩ እንዳሉም እናውቃለን ። የጀግናይቱ የመጨረሻ ቃል ምርቱ ከግርዱ እንዲለይ የሚያስገድድ፣ ሽማግሌዎቹ ሰልፋቸውን አጥርተው ለሃቅ ቆመው፣ በሃቅ እንዲመሰክሩ የሚጠራ የህሊና ደወል ነው እንላለን። ይህን ፈተና ሳያልፉም በሽምግልና ስም ትናጋቸውን እንዳይከፍቱ ተስፋችን ነው።

ጀግናይቱ እንዳለችው፣ "መልዕክቱ ግልጽ ነው። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሠላማዊ ታጋዮች። በሠላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ማድረግ የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ በተሰመረው መስመር ሳይሆን፤ ገዢው አካል ወይም ግለሰቦች በፈቀዱት ብቻ ነው" የሚል ነው። በዚህ ከልምድ አምጣ ከወለደችው ሃቅ ላይ መጨመር አላዋቂ ሳሚ እንዳያደርገን በፀጋዬ የጴጥሮስ ያቺን ሰአት ቃል "የመጨረሻውን ቃል ለጀግናዋ ተውላት" ብለን እንደመድመዋለን። ያም ቃል "በሠላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የፖለቲካ ትግል ማድረግ የሚቻለው በሕገ መንግሥቱ በተሰመረው መስመር ሳይሆን፤ ገዢው አካል ወይም ግለሰቦች በፈቀዱት ብቻ ነው" የሚል ነው። ለዚህም ደግሞ "እሺ" ወይንም "አዎ" ማለት ለእኔ እጅግ ከባድ ነው።"

## ፋሽስታዊ አገዛዝ በንጹህን .... (ከገጽ 1 የዞረ)

የተከበሩ እሴቶችን ማዋረድ የወራሪ ቡድን መለያ መሆኑን ያስታወሱት ምሁር በምርኮ የተያዘው የኢትዮድያ ህዝብ ከወራሪው የማፍያ ቡድን ለመገላገል እና የሀገሩ ባለቤት ሆኖ እሴቶቹን ጠብቆ ለመኖር በአጭር ታጥቆ መነሳት እንዳለበት አሳስበዋል።

ይህንን አሰመልክቶ ባለፉት 24 ሰዓታት በየኢንተርነቱ እየተሰጡ ካሉት በርካታ የህዝብ አሰተያየቶች ጥቂቶቹን ባልደረባችን ሳሙኤል ሉክ እንደሚከተለው ዘግቦታል።

የህዝቡ ቁጣ ግንፍል ብሎ መቀስቀሱን፤ በአብዛኛው አስተያየት ሰጪ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የመጠቃት እና መዋረድ ስሜት የሚንጸባረቅባቸው መልክቶች በብዛት በየድህረ ገጹ ላይ እየተዘገበ ነው። በትናንትናው ምሽት በሁሉም የፓልቶክ የውይይት መድረኮች አጀንዳ ሆኖ ያመሸው የዚሁ የወያኔ አዲሱ አፈና ጉዳይ ነብር። የወያኔን የአፈናና የጭፍጨፋ ተግባር በለሰለሰ ነገር ግን እራሳቸውን እንጂ ሌላውን ማሳመን በማይችል ቋንቋ ሲሰብኩ የኖሩት ስይቀር በድሪጊቱ ተሸማቀው ሲያሞጋግሱት የነበረውን የነ መለስ ዜናዊን ዲሞኪራሲ ክፉኛ ሲኮንኑት አንግተዋል። ለሎች ለዲሞክራሲ ወገንተኛ የሆኑት ደግሞ በየግላቸው ትግሉ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን የየራሳቸውን አሰተያየት በመሰንዘር ሁሉም በቁርጠኝነት እንዲህ ዓይነቱ አዋራጅና የተገዥነት ዘመን በአፋጣኝ የሚያበቃበትን ዘመን ለማምጣት መነሳት እንዳለበት ጥሪ ሲያደርጉና ወያኔን ሊገባው በሚችል ቋንቋ ለማነጋገር ለሚደረገው ሁለገብ

# ሃይለ ሀሳብ

## የመለስ ዜናዊና የግበረ- በላዎቹ ታላቅ የዘረፋ እቅድ ሲጋለጥ

**(ከዝግጅት ክፍላችን)**

ኢትዮጵያ በመለስ ዜናዊና በግብረበላዎቹ ተዘረፈች ብሎ ህዝብ ይጮሃል። የሃገሪቱን ኢኮኖሚ፣ የትራንስፖርት ክፍሉን፤ ባንኩን ኢንሹራንሱንና የመንገድና የህንጻ ስራውን፣ የአስመጪና ላኪ፣ የማምረቻና የማከፋፈፈያ ንግዱን በሙሉ የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናት በፖለቲካ ድርጅታቸው፣ በሚስቶቻቸው በዘመዶቻቸውና በቁባቶቻቸው ስም ባቆሟቸው ኩባንያዎች አማካይነት የተቆጣጠሩት እንደሆነ ሁሉም ካወቀው ሰንብቷዋል። በሃገሪቱ ውስጥ የሚከናወን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በቀጥታ በወያኔ ቁጥጥር ስር ካልዋለ በእጅ አዙር የወያኔ ባለስልጣናት ገንዘብ ከጀርባው አለ ። ወያኔ ለሚያቋቁመው የንግድ ተቋም ከግል ባለሃብቶች ጋር ለይስሙላ ሽርክና ይገባል ወይም ደግሞ የግል ባለሃብቶች ከሚያቋቁሙት የንግድ ተቋም ጀርባ ወያኔ የሚያንቀላፋ ሽሪክ ሆኖ መግባቱ የተለመደ ነው። እንዲህ አይነቱ የንግድ ሽርክና ለወያኔ ገንዘብ እስካስገኘለት ድረስ የትኛውንም የህግ የግብረገባዊነትና የሞራል ማእቀብ ለመስበር አይመለሰም። ለምሳሌ የውጋገን ባንክ አመሰራረትን መመልከቱ ይበቃል። ወያኔ በውጋገን ባንክ ምስረታ ወቅት ያሰባሰባቸው ባለሃብቶች በደርግ ግዜ በኮንትሮባንድና በህገወጥ ንግድ ተከሰው የነበሩ፣ ሀብታቸው በከፍተኛ ሙስናና ወንጀል የተገኘ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት ለመለስ ዜናዊ ሲላክለት የሰጠው ምላሽ ሪፖርቱን ተቀብሎ ካዝና ውስጥ መቆለፍ በሪፖርት አቅራቢዎቹ ዘንድ የቀረ ሰነድ እንዳለ በማለት ቢሯቸውን በሚቹ የጸጥታ ሃለፊ በክንፈ አማካይነት መስበር ማስበርበርና መውሰድ ነበር።

ወያኔ የተያያዘው አገሩን በጠመንጃ እንደወረረው ሁሉ ኢኮኖሚውንም እንደዛው መውረር ነው። ብድር ከመስጠት አንስቶ የውጭ ምንዛሪ በመፍቀድ የወያኔ ባለስልጣናት ስለሚበሉት ጉቦ፣ የተለያዩ የስራ መስኮችን ለውጭ ተቋራጮችና ኩባንያዎች በመስጠት በመንግስት ስም የሚገዙ እቃዎችን በተጋነነ ዋጋ ከውጭ ኩባንያዎች በመግዛት የወያኔ ባለስልጣናት በመሰብሰብ ላይ ስላሉትና ስለሰበሰቡት ሃብት መናገሩ ትርጉም የለውም። ምክንያቱም ተብሎ ተብሎ ያለቀለት ጉዳይ ነውና።

ይህ የሌብነትና የዘረፋ መረብ ምን ያህል የተራቀቀና የተወሳሰበ፤ ምን ያህል በዋንኛነት በዘረኛነትና በአደግዳጊነት ላይ የቆመ ለመሆኑ ዝርዝሩ ብዙ ነው። ከእዚህ ቀደም የግንቦት 7 ድምጽ የጠቀሰውን አንድ ምሳሌ ማንሳት ይበቃል። ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ ከረጅም ዘመን እስራት በሁዋላ የተፈታው የወያኔ ቁንጮ የሆነው የስብሃት ነጋ ወንድም ከጥቂት አመታት በፊት ሲሞት 50 ሚሊዮን ብር ነበረው። በአስር አመት ውስጥ የስብሃት ነጋ ወንድም ከዜሮ ተነስቶ አንዲት ከፍል ውስጥ ስልክና ጠረጴዛ ይዞ በመቀመጥ 50 ሚሊዮን ማካበት የቻለው ከወያኔ ኢህዴግ ጋር በነበረው ግኑኝነት ነው። ግንቦት 7 በሚገባ እንደሚያውቀው ከእዚህ 50ሚሊዮን ብር መሃል አምስቱ ሚሊዮን የስብሃት ነጋ ወንድም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአባ ጳውሎስ ትእዛዝ የተከፈለው ነው። በወቅቱ ለጳጳሱ አማካሪ የነበረ የጎጥ በሽታ ያልተጸናወተው ግለሰብ ይህ ገንዘብ ተሰራ ከተባለው ስራ ጋር ፈጽሞ የማይመጣጠን እንደሆነና አግባብነት የሌለው ክፍያ መሆኑን ሲያስረዳ ከጳጳሱ የተሰጠው ምላሽ ግድ የለህም ሰውየው ተጎድቷል የሚል እንደነበር ከጥቂት አመታት በፊት ይህ አማካሪ ዛሬ የግንቦት 7 አመራር አካል ለሆኑ ግለሰብ መግለጹን የግንቦት 7 ድምጽ ማረጋገጥ ችሏል።

ይህ የዘረፋ መረብ ከቀንደኞቹ የወያኔ ባለስልጣናት አልፎ፣ ኦህዴድንና ብአዴን በሚባሉ የተለጣፊ ድርጅቶች መሪዎች ውስጥም እንደ ጋንግሪን ቁስል እየተስፋፋ ይገኛል። ደርግ ወደ ኤርትራ ሲያዘምተው የዋቢ ሸበሌ ሆቴል ዘበኛ የነበረው አባዱላ ገመዳ በምርኮ ተይዞ ወያኔን ተቀላቅሎ ጄነራል መባሉ ሃገሩን ሲያስገርም፣ ዛሬ ደግሞ አሉ ከሚባሉት ቱጃሮች መሃል አንዱ ለመሆን በቅቷል። ልጆቹን ዴንቨር ኮሎራዶ ውስጥ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሲያስተምር ለአንደኛው ልጁ የልደት በአል ስጦታ የሰጠው የ800 ሽህ ብር ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ነበር። ማንን አንስተን ማንን እንተዋለን። እንዲያው ዝም ብለን ይህ ዘረፋ አልፎ አልፎ የሚከሰት ሳይሆን የስርአቱ ቋሚ ቀለብ ነው ብለን እንለፈው እንጅ።

ሌለው ጸሃይ የሞቀው የዘረፋ ተግባር ወያኔዎች የአዲስ አበባንና የሌሎችን ከተሞች መሬት በመንግስት ባለቤትነት ስም የግላቸው አድርገው ሲቀራመቱት መክረማቸው ነው። መሬት የመንግስት ነው ስለእዚህም ለባለስልጣናቱ ከእዚህ መሬት እየተቦጨቀ ይሰጥ በሚል ትእዛዝ የወያኔ ባለስልጣናትና አብረዋቸው የተሰለፉ ሆድ አደሮች ውድ የከተማ ቦታዎችን በመውሰድ በአንድ ምሽት ሚሊዮነሮች ሆነዋል። 5ና 10 ሽህ ብር የማያወጣ ቤት በእነዚህ በነጻ በተሰጡ መሬቶች ላይ በመስራት፣ መልሶ መሬቱን በሚሊዮኖች ብሮች በመሸጥ የከበሩ የወያኔ ጄነራሎችንና ሚኒስቴሮችን ስም መዘርዘር ለግንቦት 7 የሚዳግተው አይደለም። ከእነዚህ ሚሊዮኖሮች መሃከል ጥቂቶቹ በወያኔ ክፍፍል ከኢህአዴግ የተባረሩትን ግለሰቦች ይጨምራል። ከእዚህ ውጭ ደግሞ በእዚህ በነጻ በሚሠጥ ውድ ቦታ ላይ ቤት ሰርተው ከገበያ የኪራይ ዋጋ በላይ በውጭ ምንዛሪ ለፈረንጆች በማከራየት የቤት ኪራይ ብቻ ሳይሆን ከነጮቹ በኪራይ ስም የተዘዋዋሪ ጎቦ የሚሰበስበው ሚኒስቴርና ጄነራሉ ብቻ ሳይሆን ከእዛም በታች ያሉ ሹመኞች ሆነዋል። የመጠቃቀሙ ስራ ምን ያህል እስከታች እንደወረደ ለማውቅ የወያኔ ባለስልጣናት ጠባቂ ዘበኞች ወይም በወያኔ አጠራር ዋርድያዎችና ሹፌሮች ሳይቀሩ ለ12 ሰዎች ቤት መስሪያ የሚሆን የኮንዶሚኒየም ቦታ በግላቸው በመውሰድ እያንዳንዱን የአፓርትመንት መገንቢያ ለአስራ ሁለት ከውጭና ከሃገር ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች በ60ና 70ሽ ብር በመሸጥ በአንድ ሳምንት ውስጥ የ700ና 800 ሽብር ጌቶች ለመሆን በቅተዋል። እንዲያው በደፈናው ዘረፋው ተነግሮ አያልቅም። የሚገርመው ግን ይህ ዘረፋ ወደፊት ወያኔ ካቀደው ከፍተኛ የዘረፋ እቅድ ጋር ሲነጻጸር ውቂያኖስ ውስጥ የተጣለ ጠብታ መምሰሉ ነው። የወያኔው ቀጣይ የዘረፋ እቅድ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ዘረፋ በኢትዮጵያ ብር ሳይሆን የወያኔ ባለስልጣናትን በዶላር ቢሊዮነሮች ለማድርግ የታቀደ ነው። ይህንን ይመስላል።

በአለማችን የአየር ጠባይ መዛባት፣ የህዝብ ብዛት ቁጥር መጨመር፣ ብዙ የህዝብ ብዛት ያላቸው ቻይናን ህንድን የመሳሰሉ ሃገሮች የኢኮኖሚ እድገትና ይህ ያስከተለው የዜጎቻቸው የፍጆታ አቅም ማደግ፣ ነዳጅ ከሰብልና ከእጽዋት ለማምረት የተጀመረው አዲስ ቴክኖሎጂ በአንድ ላይ ተደምረው በአለማችን ከፍተኛ የሰብል እጥረትና የዋጋ ንረት ማስከተላቸው ይታወቃል። ይህ ሁኔታ እየባሰበት እንጂ እየተሻሻለ እንደማይሄድ ኢኮኖሚስቶችና የአከባቢ ጥናት ኤክስፐርቶች የሚምሉበት ጉዳይ ሆኗል። ይህ እውነት ለብዙ ግዜ ሀብታም ሀገሮችና ሃብት ያላቸው ግለሰብ ኢንቨስተሮች ብዙም ትኩረት ሰጥተውት ወደ ማይታወቀው የእርሻ ስራ ፊታቸውን እንዲያዞሩ አድርጓቸዋል። የአለም መንግስታት ህዝባቸውን ለማብላት ብቻ ሳይሆን እየተወደደ የሚሄድን የእርሻ ሸቀጥ መቆጣጠር በኢኮኖሚ መስክ ማሳደር የሚችሉትን ተጽእኖ ብቻ ሳይሆን ስትራተጂክ የሆነ የፖለቲካ አቅም ይሰጣል የሚል እምነት እንዲይዙ አድርጓቸዋል።

ይህንን አስመልክቶ ከጥቂት ሳምንታት በፊት የግንቦት 7 ድምጽ የሎስ አንጀለስ ታይምስ የተባለውን ጋዜጣ በመጥቀስ ባቀረበው ዜና የአለም ሀብታሞች የደሃ ሃገሮችን በተለይ የአፍሪካን ደሃ ህዝብ መሬት በሙስና በተጨማለቁ የየሃገሩ መሪዎችን አማካይነት እየተቀራመቱ ወደ እርሻ ንግድ እየገቡ እንደሆነና በእዚህ ረገድ የእርሻ መሬት እንደወርቅ ተፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ገልጾ ነበር። የሎስ አንጀለስ ታይምስ ከእዚህ ጋር አያይዞ ባቀረበው ዜና በአለም ላይ መሬታቸውን ለውጭ ባለሃብቶች ለመሸጥ ከሚንቀሳቀሱት ሃገሮች መሃከል አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነችና የመለስ ዜናዊ ደላሎችም በዋናዎቹ የአረብ ሀገሮች መዲናዎች እየተዘዋወሩ ሃብታም አረቦችን መሬት ከኢትዮጵያ ወስደው በእርሻ ስራ እንዲሰማሩ የሚደልሉ ደላሎችን መቅጠሩን ጋዜጣው ማተቱን ግንቦት 7 ድምጽ አስደምጦን ነበር። ጋዜጣው በእዛው ገጽ ላይ የአለም ሃብታሞች የአፍሪቃን ወርቅ፣ አልማዝ፣ ሌላውን ማእድንና ነዳጁን መጠው በመጨረስ ላይ መሆናቸውንና አሁን ደግሞ ይህ የራሱን ህዝብ መመገብ ካልቻለ ክፍለ አህጉር የእርሻ ሰብል በማምረት የእርሻ ውጤት ለምእራብና ለአረቡ አለም ለመላክ የሚደርጉት ሙከራ አደገኛና አሳፈሪ ነው ብሎ ኮንኖት እንደነበር የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ የገለጸው ጉዳይ ነበር። ጉዳዩ ያሳሰበው የዘገባው ጸሃፊ ይህ ሃብታሞች በደሃ ሃገሮች የሚያደርጉት መሬት የመቀራመት ሽሚያ የሃገሬውን ህዝብ ጥቅም የማያስከበር፣ ሃገሬውን በገዛ ሃገሩ በሁለተኛ ደረጃ እንዲታይ ሊያደርግ የሚችል መሆኑን ማስረጃ በመጥቀስ ለመግለጽ መሞከሩን በግንቦት 7 ደምጽ ማቅረባችን ይታወሳል።

በቅርቡ ደግሞ የእንግሊዙ ቢቢሲ ቴሌቪዥን በኢትዮጵያ ጎረቤት በሆነችው ሱዳን ውሰጥ በእርሻ ስራ ብቻ ላይ ባለፉት ስድስት ወራት የአረብ ሃበታሞች 9 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ኢንቨስት ማድረጋቸውን በመግለጽ የአፍሪቃን መሬት ለመቀራመት ሩጫው መጀመሩን በመግለጽ የሎስ አንጀለስ ታይምስ አቅርቦት የነበረውን ዘገባ አጠናክሮታል። ባለፉት 3 ሳምንታት ውስጥ ሮይተር እንደዘገበው የኳታር ሃብታሞች 50 ሽህ ሄክታር መሬት ከኬንያ መንግስት በመውሰድ የእርሻ ስራ ለመጀመር መንቀሳቀሳቸውን ይህ የእርሻ ስራ ወደፊት በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋቱን ግምት ውስጥ

አስገብተው የኳታር መንግስት 2.3 ቢሊየን ፓውንድ ወጪ በማድርግ ከኬንያ ወደ ውጭ ለሚልከው የእርሻ ውጤት የሚያገለግል የወደብ ስራ ለማከናወን መወሰኑን ገልጾዋል።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው የአፍሪካ መሬት በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ነው። ወደ ሃገራችንም ስንመለስ የወያኔ አዲስና አስፈሪ የሆነው የዘረፋ እቅድ የተሳሰረው ከእዚህ ጉዳይ ጋር ነው። ወያኔ በከተማ እንዳደረገው በገጠር የሚገኘውን ለዘመናዊ እርሻ የሚሆን መሬት ከረጅም ግዜ ጀምሮ ምንም ስራ ሳይሰሩበት ለተቀመጡ የመንግስት ባለስልጣንና ሽሪኮቻቸው ሲያከፋፍል መቆየቱ ግልጽ ነው። ሃገሬው በከተማ ቦታ ላይ በሚካሄደው ዘረፋ ላይ ትኩረቱ ተሰቦ በሚጮህበት ወቅት ወያኔ ኢህአዴግ የገጠሩን ቁልፍ መሬት ለራሱ ድርጅትና ለስርአቱ ባለሟሎች አከፋፍሎ ጨርሶታል። በመላው አለም የተበተነው ስደተኛ ኢትዮጵያዊ ራሱን ጠቅሞ ሃገሩን ለመጥቀም በተለያዩ ግዚያት ያቀረባቸውን የእርሻ መስክ ኢንቨስትመነት ስራዎች በማደናቀፍ የሚታወቀው ወያኔ በአረብ ሃገሮች እየዞረ መሬት ግዙኝ የሚል ድለላ ለማረግ የተነሳው ኢትዮጵያዊ የሆኑ ዜጎች በኢኮኖሚ አንዲደራጁ የማይፈልግና ለአረቦቹ ለመሸጥ ካሰበው መሬት ላይ የሚያገኘውን ዶላር የሚያጎሉበት መሆኑን በመረዳቱ እንደሆነ ታውቋል።

የወያኔ አገዛዝ ዘረኛ የሆነ ፖሊሲ በክልል አስተዳደሮች ውስጥ እንዲስፋፋ በማድርግ አንድ ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የሃገሪቱ ክልል መዋእለ ነዋዩን በስራ ላይ በማዋል ራሱን ጠቅሞ የአካባቢውን ህዝብ እንዳይጠቅም የኢንቨስተሮችን የዘር ጀርባ በክልሎች በለስልጣናት እንዲመረመር መመሪያ በመስጠት የኢንቨስትመንት እንቅፋት እንደሆነ ይታወቃል። በአንድ በኩል ፈረንጅንና አረቡን ናና መሬት ግዛ፤ ኢንቨስት አድርግ እያለ የሚለምነው ወያኔ በሌላ በኩል ገንዝብ ያላቸው የየክልሉ ተወላጆች ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን በኢንቨስትመንት ስም ባሪያ ሊያደርጉህ ነው በማለት ህዝብን በዘር እያነሳሳ ኢትዮጵያውያንን በገዛ ሀገራቸው በመረጡት ቦታ ኢንቨስት እዳያደርጉ የሚያደርግ ጸረ- ኢትዮጵያ ፖሊሲ እንደሚከተል ግልጽ ነው። ይህ አይነቱ ፖሊሲ ዋና አላማው የሚገለጠው ህዝብን በመከፋፈል የስልጣን እድሜን ማራዝም፤ ብቻ ሳይሆን በገጠር መሬት ላይ ወያኔ ሊያካሂደው ከተዘጋጀበት የዘረፋ እቅድ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው።

በሱዳን በኩል ከሚገኘው የሃገራችን ክፍል ሰፊና ለም መሬት መሃል ወያኔ ለምን በአሁኑ ግዜ መሬት ቆርሶ ለመስጠት ወሰነ የሚለው አስገራሚ ጥያቄ ወያኔ እንደሚለው ቀድሞ የነበረን የዳርድንበር ጉዳይ መልክ ለማስያዝ ሳይሆን ጉዳዩ በቀጥታ የተሳሰረው የአረብ ሃገሮች በሱዳን ውስጥ ለእርሻ ስራ ማፍሰስ ከጀመሩት አጅግ ከፍተኛ የሆነ መዋእለ ነዋይ ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ግልጽ ሆኗል። የአረብ መንግስታትና ባለሀብቶች በስድስት ወር ብቻ 6 ቢሊዮን ዶላር ሱዳን ውስጥ በእርሻ ላይ አዋሉ ማለት አጠቃላይ ኢንቨስትመንታቸው በመቶ ቢሊዮኖች የሚቀጠር ዶላር ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ከባድ አይደለም። ወያኔ ለሱዳን የሰጠው መሬት ተራ ስጦታ ሳይሆን እጅግ ከፍተኛ የሆነ የአሜሪካ ዶላር በወያኔ ባለስልጣናት ይህንን መሬት ለአረቦች ለማኮናተር በሚፈለገው የሱዳን መንግስትና መሬቱን በሚፈልጉት አረቦች አጅ መሃከል መቀያየሩን ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። እነዚህ ውስጥ አዋቂዎች አንደሚገምቱት የእዚህ ገንዘብ ብዛት ወያኔ እስከዛሬ በሃገራችን ላይ ከዘረፈው ሃብት ሁሉ የላቀ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአረብ ሃገር የተሰማሩ ደላሎች ቀደም ብለን የጠቀስነውን የወያኔ ባለስጣልናትና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው በነጻ በኢንቨስተርነት የያዙትንና እስካሁን ምንም ስራ ሳይሰሩበት የተቀመጡበትን መሬት ለመቸብቸብ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቷል ይባላል። ይህ የደላሎቹ ጥረት በስራ ሲተረጎም የወያኔ ባለስልጣናትና ተላላኪዎቻቸው፣ በአንድ ጀንበር በአሜሪካን ዶላር የብዙ መቶ ሚሊዮኖች ጌቶች ሆነው ያርፉታል። ይህ ገንዝብ የወያኔ ባለስልጣናት ኢትዮጵያውያንን አፍኖና አዋርዶ ለመግዛት፣ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውንና የጀሌዎቻቸውን የተቀናጣ ህይወት ለማስቀጠልና የተቀረውን ዜጋ በፍርፋሪ ለቃሚነት በውሻነት ደረጃ ለመግዛት የሚያስችለን አቅም ይሰጠናል ብለው ጉራ መንፋት መጀመራቸው በአገዛዙ ስርአት ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችን በመጥቀስ የግንቦት 7 ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቀዋል።

እነዚህ የውስጥ ምንጮች እንደሚሉት ዛሬ በሃገራችን ላይ የነገሰውን ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ ዘረኛ ዘራፊ የሆነ ሃይል ህጋዊ መንግስት በማድረግ የተለያዩ መንግስታትና ባለሃብቶች ከአገዛዙ ባለስልጣናት ጋር የሚገቡት ስምምነት የስርአቱን እድሜ ማራዘሚያ እየሆነ መጥቷል። ይህ ከወያኔ ጋር የሚደረግ የተለያዩ ሃገራትና የባላሃብቶች ውልና ስምምነት ወያኔ በሃገርና በወገን ላይ የሚፈጸመው ወንጀል አካል መሆኑን እነዚህ ሀገራትና ባላሀብቶች በማያሻማ ቋንቋ ሊነገራቸው ይገባል ይላሉ። እነዚህ ሃይሎች ዛሬ ህገወጥ በሆነ መንገድ ከተዘፈዘው አገዛዝ ጋር የሚገቡት ውል ነገ የህዝብ ውክልና ያለው መንግስት ሲመጣ ሊከበር የማይችል መሆኑን አሁኑ እንዲያውቁት ግንቦት 7ና ሌሎችም ተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ አቋም ወስደው ለአለም አቀፍ ማህበረሰቡና ሌላውም ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይኖርባቸዋል በማለት በወያኔ አገዛዝ ውስጥ ያሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አበክረው ያሳስባሉ።

የዝግጅት ክፍላችንም የግንቦት 7 አመራር በእዚህ ጉዳይ ላይ እንዲያስብበት ማሳሰቢያ እያስተላለፈ፣ የሃገራችን ህዝብም ወያኔ በቀጠይነት የደገሰውን የዘረፋ ድግስ መብላት እንዳይችል አምሮ በመታገል ሀገሩን በልተው ከማይጠግቡ የቀን ጅቦች ነጻ በማውጣት የሃገሪቱም ሃብት ጥቂት በዘር የተደራጁ አምባገነኖችና አደግዳጊዎቻቸው ብቻ የገነት ሕይወት የሚኖሩት ሳይሆን የሃገሪቱ ዜጎች በሙሉ በጋራ የሚገለገሉበት ማድረግ ይኖርበታል ይላል።

---

## ፋሽስታዊ አገዛዝ በንጹሀን .... (ከገጽ 2 የዞረ)

በፅሁፍ በድህረ ገጽ ላይ በተለያዩ ሰዎች ከተሰጡት አስተያየቶች ድግሞ ታዋቂው ፕሮፌሰር ቴዎድሮስ ኪሮስ የመሪዎቻችንን መታሰር በማንኛውም መልኩ መታገል ይገባናል: ይበቃል ይበቃል!! ከዚህ በላይ ልንታገስ አይገባም ማለታቸው ታውቋል። አቦ ቢቂላ የተባሉት ሰው ደግሞ "ወያኔ ተሰፋ መቁረጡን በሃይድ አስመሰከረ! ራሱን በራሱ ከስሩ አነቃነቀ። ብቀላው ሌሎችንም ይጠብቃል። ቀሪዎቹ ተቃዋሚዎች እና በመላው አለም የምንገኝ ኢትዮጵያውያንም ይህን ድርጊት ማውገዝ አለብን። ተሰፋ የቆረጠ የበሰበሰ አመራር ለአገራችን አያስፈልጋትም። በግንባር ለሚፋለሙ ታጋዮች ዛሬ ነገ ሳንል የተቻለንን እናድርግ። ፍርድ ለመለስ ጎጠኛው አሁኑኑ!!!" ብለውል።

ሌላው አስተያየት ሰጪ ማሩ ቀመስ በቅርብ ነጻ መውጣታችን አሌ የማይባል ነው ይሉናል። "እናንተ ደም የለመዳችሁ ሰይጣናት ምሳችሁን እስኪታገኙ ድረስ ነው። የወያኔ ቀናት እየተቆጠሩ ነው። ምን አል ማሩ ቀመስ በሉኝ! በዚች ሁለት አመት ውስጥ አገራችንን ኢትዮጵያን ነጻ እናወጣለን።"

ሰቆቃው በዛ የተባሉ አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው ወያኔ አዋረደን እንነሳ ይላሉ፤ "እንነሳም ወይ? ምን እስኪያደርጉን ነው የምንጠብቀው? አዛውንት የሐገር አድባር ባደባባይ መደብደብ አረ ተዋረዱን ይሄ ሁሉ እብሪት አርፎ የተቀመጠውን ሕዝብ ምን ትሆናለህ? ማለት ነውና አረ በቃን እንበል:: ወደናቸው የተገዛን ምስሎዋቸው ይሆን? ሕዝባችን በቃኝ በል። በብርቱካናችን ከመጣሁ ከዚህ በላይ ተግስት የለንም በልና ሆ ብልህ ተነስ ተነስ እንጂ.......................... ኢትዮጵያ ሐገራችንን አምላክ ይጠብቅልን። ብርቱካንንም እንዲሁ።"

አሚር የተባሉ አስተያየት ሰጪ በብርቱካን መታሰር አለመገረማቸውን እና መፍትሄው ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ማናገር ነው ብለዋል።

"ብዙም አልደነቀኝም። ወያኔ ደም ለምዱዋል እናም ያን ካላገኘ አያሳርፈዉም። ለዛም ነው ከአሁን በሁዋላ እነሱን እየሸነገሉ መኖር የማያዋጣው። በማይገባቸው ቅዋንቅዋ መረዳዳት አይችሉም ስለዚህ በሚገባቸው ነገር ማናገር ብቻ ነው ያለው አማራጭ። እናም እባካችሁን ሰቆቃ እና መከራ ያበቃ ዘንድ ሁላችንም ሃሳባችንን: ጉልበታችንን: ገንዘባችንን እና ጊዚያችንን አስተባብረን ለማይቀረው የአገራችንና የህዝባችን ነጻነት እንነሳ። ብርቱካንና ኢጋሮቻ አላህ እናንተ ጋ ይሆን ዘንድ እንጸልያለን ማድረግ የሚገባንንም ከማድረግ ወደሁዋላ አንልም።"

ሩፍኤል የተባሉ አስተያየት ሰጪም እንደተቀሩት ሁሉ ለሰላማዊ ትግል ምንም መፈናፈኛ እንደሌለ እና ለማይቀረው ትግል እንነሳ ብለዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።**

በዚሁ መሰረት ከአሁን በኋላ **በ7485 KHZ በ41 ሜትር ባንድ** እና **በ9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።